በወያኔና በሱዳን መከላከያ መኮንኖች ጥብቅ ሚስጢራዊ ስምምነት ተደረገ፤

ዘመናዊ የጦር የሚሳኤል ማስተኮሺያ መሳሪያ አዲስ አበባ ገባ፤
የውጭ ሃገር ዜግነት ያላቸው ወታደራዊ መኮንኖች ከጦር መሳሪያው ጋር አብረው መግባታቸው ተነገረ፤

የወያኔው ተላላኪ እና የፍትህ ሚኒስትር የነበረው አሰፋ ከሲቶ በውርደት ከመኖሪያ ቤቱ ተባረረ፤

የቃሊቲው እስር ቤት በእስረኞች አመጽ ሲታመስ ሰነበተ፤በድብደባ የተጎዱ እስረኞች የህክምና እርዳታ እንዳያገኙ ተከለከሉ፤
ማንነታቸው ያልታወቁ አንድ መቶ እስረኞች በድብቅ ቃሊቲ እስርቤት ገቡ፤

የወያኔው ቡድን ሰሞኑን ከሱዳን ጋር አዲስ ወታደራዊ ስምምነት በምስጢር መፈራረሙን ተከትሎ ግብጽ ማኩረፉዋን ለስዩም መስፍን ቢሮ ቀረቤታ ያላቸው ዲፕሎማቲክ ምንጮች አስታወቁ ::

ከቅርብ ግዜ ወዲህ በተለይ ኣለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት በሱዳኑ ፕሬዝደንት አልበሽር ላይ የእስራት ኦራንት መቁረጡን ተከትሎ በወያኔና በሱዳን መካከል እከክልኝ ልከክልህ በሚል ፍቅር እየናወዙ መሆኑን ያመለከተው ዘገባ የውስጥ ችግሮቻቸውን ለማርገብ በሚል ሽፋን ሁሉ አቀፍ መግባባት ላይ መድረሳቸውንና በተለይ በወታደራዊ መስክ እጅግ ጠንካራ ስምምነት የተፈራረሙ መሆናቸውን አስረድቶዋል ::

የሱዳኑ ፕሬዝደንት አልበሽርና የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በተገኙበት የሱዳኑ የመከላከያ ሚኒስትርና የወያኔው ጄኔራል ሳሞራ የኑስ በወታደራዊ ግኑኝነት ዙሪያ ጥልቅ ውይይት ካደረጉ በሁዋላ ስምምነት ላይ የደረሱ ከመሆኑም በላይ ባለፈው ሳምንት ደግሞ ስለተግባራዊነቱ ተመካክረው በፊርማቸው አረጋግጠዋል ::

የወያኔ ቡድን የድንበር ላይ እንቅስቃሴዎችን ለመቁዋቁዋም ብሎም ለማስወገድ በመቻኮል የሱዳኑን የትብብር ስምምነት በአስቸኩዋይ ተግባራዊ እንዲሆን ታስቦ የሱዳኑን የመከላከያ ሚኒስትር ወደ አገር ውስጥ አስጠርቶ በሚስጢራዊ ሁኔታ መፈራረማቸውን የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል

በሁለቱ አገራት መካከል በከፍተኛ የጦር አለቆች በኩል እየተፈራረሙ ባሉበት ወቅት የወያኔው ቡድን ከ 30 በላይ ሚሳኤል ተሸካሚና በላያቸው ላይ ማስተኮሺያ ኮምፒውተር የተገጠመላቸው ዘመናዊ ተንቀሳቃሽ መኪኖችን በድብቅ ወደ ቀድሞ አየር ሃይል ማረፊያ ግቢ ውስጥ አስገብቶዋል ሲል የአይን እማኞችን የጠቀሰው ዘገባ አስረድቶዋል

ለዚሁ ሚሳኤል ማስተኮሺያ ኮምፒውተር የተገጠመላቸው ሚሳኤል ተሸካሚ ባለ 32 አጫጭር ጎማ የተገጠመላቸው መኪኖች በውድቅት ለሊት ከህዝብ እይታ እየተሰወሩ በድብቅ የቀድሞ ምድር ጦር ግቢ ውስጥ የገቡ ሲሆን ከዚሁ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ጋር ቁጥራቸው እጅግ በርካታ አዳዲስ ስሪተ ስማቸው ቮልቮ የሆነ ወታደራዊ መሳሪያዎችን መጫኛ ከባድ መኪኖችም አብረው መግባታቸውን እነዚሁ የአይን እማኞች አስረድተዋል

በጦር ሜዳም ሆነ በሰላማዊ ቦታ ከባድ የጦር መሳሪያዎችን ከጭነት ላይ ለማውረድና ለማጫን የሚያግዙ ሌሎች አዳዲስ መሳሪያዎችም ከእነዚሁ የጦር መሳሪያና ተሽከርካሪዎች ጋር አብረው የገቡ ሲሆን ይህንን ሁሉ ቅድመ ዝግጅት ወያኔ እያደረገ ያለው በጎንደር በኩል ተጠናክሮ እየመጣ ላለውና በየእለቱ ግዳይ ለሚቀናው

የታጠቀ የተቃዋሚ ሃይል መምቻና ለሻእቢያ ማስፈራሪያ ሊሆን እንደሚችል አንድ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈቀዱ ከፍተኛ የጦር መኮንን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል

ሀገሪቱዋ ከምትችለው አቅም በላይ ወጪ መድቦ ከፍተኛ የህዝብና የአገር ሃብት እያባከነ ያለው ጠባቡ እና ዘረኛው የወያኔ ቡድን እርስ በእርስ የተዘፈቀበት ችግር እልባት አጥቶ እያመሰው በሚገኝበት በዚህ በአሁኑ ወቅት በውጭ ደግሞ ከታጠቁ የተቃዋሚ ሃይሎች በሚሰነዘርበት ጥቃት ጫናውን ለመቋዋቋዋም ይረዳኛል በሚል ላይ ታች እያለ፤ መሆኑንም አራት ኪሎና ሰበታ ከተማ ላይ ጽህፈት ቤትህን እንገነባለን ከሚሉት አለቅላቂዎቹ ቅርበት ያላቸውን ወገኖች ጠቅሶ ዘገባው አስረድቶዋል

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በበኩሉ በብአዴን ላይ እምነት በማጣቱና መፈንቅለ መንግስት ያደርጉብኛል በሚል ስጋት ተወጥሮ እንደወትሮው በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ መዙዋዙዋር ሳይችል ቀርቶ የነበረ ሲሆን ሰሞኑን ብዙም ሳይርቅ በአፍሪካ ውስጥ በራሱ ግዜ ያለ ኦፊሴሊያዊ ጥሪ በጉብኝት ስም ደርሶ የመጣ ቢሆንም የቤተ መንግሰቱን ጥበቃ በአራት ዙር እንዲጠናከርና ለታዛዡ ሳሞራ የኑስ አደራ ሰጥቶ እንደነበር አራት ኪሎ የሚገኘው የሚኒሊክ ቤተ መንግስት ውስጥ አዋቂዎች ያስረዳሉ።

በዓባይ ወንዝ የተነሳ አይናቸውን ከተከሉ የማይነቅሉት ፤ ለዚህ ሲሉ የተለየ ተዋጊ ሃይል በልዩ ሁኔታ አሰልጥነውና ዘመናዊ የጦር መሳሪያ አስታጥቀው ከዛሬ ነገን በመጠባበቅ ላይ የሚገኙት ፤ ያጠለቁት ወታደራዊ ጫማቸው እንኩዋን ሳይፈታ በዝግጁነት ላይ የሚገኙት ግብጻውያንን የሰሞኑ የወያኔና የሱዳን ወታደራዊ ስምምነትን በንቃት እንዲመለከቱት  ያደረጋቸው መሆኑን አዲስ አበባ ለሚገኘው የግብጽ ኤምባሲ እና በስዩም መስፍን ቢሮ ውስጥ የሚገኙ ለአካባቢው ወታደራዊ አታሼዎች ቅርበት ያላቸው ምንጮች ማጋለጣቸው በዘገባው ተመልክቶዋል

በሰራዊቱ መካከል ክፍፍል እንዲፈጠር በማሰብ በአንድ ወገን እና በአንድ ብሄር ብቻ ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ በማድረግ እና ምንጠራ በማካሄድ ስራ ተወጥሮ የሚገኘ ው የወያኔው አገዛዝ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የጦር አለቆችን እና የበታች ሹማምንቶችን ከያሉበት እያፈሱ ለእስር በመዳረጋቸው ሰራዊቱ በማኩረፉ በየትኛውም ግንባር ውጊያ ቢገጥም ውጤታማ እንደማይሆን የተረዱት እነመለስ ዜናዊ በአገርና በህዝብ ገንዘብ እጅግ ውድ የሆኑ የጦር መሳሪያዎችን እየሸመቱ ወደ አገር ውስጥ እያስገቡ ከመሆኑም

በላይ ከእነዚሁ የጦር መሳሪዎች ጋር የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ወታደራዊ መኮንኖች መግባታቸውንም ዘገባው ጨምሮ ገልጦዋል

አሁን ባለው ተጨባጭ የሰራዊቱ አቋዋም ላይ እነመለስ ዜናዊ አመኔታ በማጣታቸው ሰራዊቱን አንዱን ክፍል ወደ ምስራቅ ፤ የምስራቁን ወደ ሰሜን ፤ የሰሜኑን ወደ ምእራብ እያመሰቱትና እየበወዙት ሲሆን በዚህም አልሆን ስላላቸው የመጨረሻው አማራጫቸው ለሱዳን እጅ መስጠት ብቻ በመሆኑ ለመንበርከክ ከመገደዳቸውም በላይ አገሪቱ በመብራት ሃይል እጦት እየተቸገረችና ጨለማ ወርሶዋት በምትገኝበት በአሁኑ ወቅት ለሱዳን የሃያ አራት ሰዓት የመብራት ሃይል እንድታገኝ ማድረጋቸው ለቤት ቀጋ ለውጭ አልጋ እንዲሉ የልምምጣቸው አንድ አካል ነው ሲል ዘገባው አስረድቶዋል

በሌላ ዜና የወያኔ ቀንደኛ ባለስልጣን የነበረው እና ለይስሙላው የብሄር ብሄረሰቦች ስብጥር ማሳያ ነው ተብሎ በኮታ ማሙዋያነት ለፍትህ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው አሰፋ ከሲቶ ከሚኖርበት መኖሪያ ቤት በፖሊስ ተገድዶ እንደተባረረ ከአዲስ አበባ የመጣው ዘገባ ገለፀ

በ1997 ዓ.ም. መለስ ዜናዊ የህዝብን ድምጽ ከኮሮጆ ውስጥ ገልብጦ ከዘረፈና በጠብ መንጃ ሃይል በግድ መንግስት ነኝ ብሎ የራሱን ካቢኔ ባቋዋቋዋመበት ወቅት የፍትህ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው ሆድ አደር አሰፋ ከሲቶ ለአራት አመታት ከነበረበት የሚኒስትርነት ወንበር ተባርሮ በአሁኑ ሰዓት የሙቶ አለቃ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ልዩ አማካሪ ተብሎ የተቀመጠ ቢሆንም ባለፈው ሳምንት መባቻ ላይ ከሚኖርበት በፖሊስ ተገድዶ እንዲወጣ መደረጉን የገለጸው ዘገባ በተደጋጋሚ ግዜ ቤቱን እንዲለቅ ተጠይቆ የነበረ ቢሆንም እና ይህንንም መለስ ዜናዊ እንዲያውቀው ተደርጎ የነበረ ቢሆንም በሙቶ አለቃ ግርማ አማላጅነት መቆየት ችሎ ነበር ምን ዋጋ አለው እንደ ሸንኮራ እየመጠጠ መትፋቱን የሚያውቅበት ወያኔ ዛሬ ቤት አልባ አድርጎ አሽቀንጥሮ ጥሎታል ሲሉ ሁኔታውን የሰሙ ታዛቢዎች ተችተዋል

ላፍቶ ክፍለ ከተማ ብስራተ ገብርኤል አካባቢ በሚገኘው እና ከህዝብ ተነጥቆ በተሰጠው ቪላ ቤት ውስጥ ሲንደላቀቅና አለሙን ሲቀጭ የነበረው ይህ ሆድ አደር ክብሩንና ስብእናውን ባዋረደ መልኩ ሰኔ አንድ ቀን 2001 ዓ.ም. ክረምት በገባ በመጀመሪያው ቀን በእለተ ልደታ ተባርሮዋል በእርግጥም ለእርሱ ሰኔና ሰኞ ሆኖበታል

በስብሻለሁ ግን ታድሻለሁ እያለ ለኖረ በህዝብ ለተጠላው ወያኔ ወገቡ እስኪሰበር እያጎበደዱ ስልጣን ላይ የሚወጡት አሰፋ ከሲቶና መሰሎቹ የስልጣን ወረታቸውን በቅጡ አጣጥመው ሳይጨርሱ እንደ አሮጌ ቁና በየስርቻው እየተወተፉና እየተወረወሩ መጣላቸው እየታየ ሲሆን ዛሬም ወደፊትም የወያኔ ቡድን ከተጠቀመባቸው በሁዋላ ተመሳሳይ እርምጃ መውሰዱ ጥርሱን የነቀለበትና የተጠናወተው አባዜ በመሆኑ አያስደንቀንም ያለው የደረሰን ዘገባ አሁንም በስልጣን ላይ አለን ብለው የሚሉት ሆድ አደር ህሊና ቢስ ስግብግብ ባለስልጣናት እንደ አሰፋ ከሲቶ መወርወራቸው እና ሰበብ ተፈልጎ ዘላለማዊ መኖሪያቸው ወደሚሆነው ዘብጥያ መጣላቸው አይቀሬ መሆኑን የሚናገሩ ወገኖችን ጠቅሶ ዘገባው አብራርቶዋል

ህዝባቸውን ለወያኔ አገዛዝ ባሪያ እንዲሆን እያደረጉ ለእለት ጥቅማቸው እያጎበደዱና እየተንበረከኩ ያሉት ምድረ ሆድ አደር ህሊና ቢሶች ራሳቸውን አዋርደው ወክለንሃል ያሉትን ህዝብ ጭምር የሚያስደፍሩ ወርደት ቀለባቸው የሆነ ካድሬዎች ሁሉ የህዝብን በትር መቅመሳቸውና በለበቁ መቀጣታቸው አይቀሬ ቢሆንም ምንአልባች መካሪ እና ዘካሪ ወገን ዘመድ አግኝተው ከእኩይ ድርጊታቸው መመለስ ቢወድዱ ይቅር ባይ ህዝብ በእቅፉ ሊያገባቸው እንደሚችል መናገር ነቢይ መሆንን ባይጠይቅም ይህ ባይሆንም ወያኔ ራሱ እያንጉዋለለ መድረሻ እስከሚያጡ ድረስ ጥላቸውን እየተከተለ የሚያሳድዳቸው መሆኑንም ጥቅም በደፈነው ህሊናቸው ለአፍታም ቢሆን ማሰብ ተገቢነቱ አያጠያይቅም ሲል ይኸው ዘገባ ያስረዳል

የወያኔው ቡድን በመከላከያ እና በካድሬዎቹ ውስጥ በተከሰተው የፖለቲካ ቀውስ የተነሳ ከፍተኛ አጣብቂኝ ውሳጥ ባለበት በዚህ ሰዓት በየእስር ቤቱ ታጉረው ባሉት ምስኪን ዜጎች ላይ በሚያደርሰው ግፍ የተነሳ ከልክ ቢያልፍባቸው ሰሞኑን ብሶታቸውን በተቃውሞ መግለጽ መጀመራቸው ተሰማ

በአዲስ አበባ ቃሊቲ የሚገኘው እስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደተነሳና በአጠራሩ ዞን ሁለት በተባለው ግቢ ውስጥ የወያኔ ንብረት የሆኑ በሙሉ በእስረኞች እንደወደሙ ታውቆዋል

ሰኔ አንድ ቀን 2001 ዓ.ም. ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ላይ በግቢ ውስጥ ያሉ ፖሊሶችና የወያኔ አደራ ጠባቂ ነን የሚሉ ሹመኛ ካድሬዎች እንደለመዱት በእስረኞቹ ላይ የማንከራተት ተግባራቸውን ሊያከናውኑ በሚዘጋጁበት ወቅት እስረኞቹ የጋራ አቋዋም በመውሰድ በእስራት ላይ ሌላ እስራት የለምና አንገላታም የሚል የጋራ አቋዋም

በመያዛቸው ፖሊስ  በዱላ የሃይል እርምጃ በመውሰድ በበርካቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳት መድረሱን ከማወቅ ተችሎዋል

በሰዚሁ የሰኔና ሰኞ ግጭት ተከትሎ በእስረኞቹ ላይ የደረሰውን ድብደባ የተቃወሙትና የሌላ ዞን እስረኞች ፖሊሶቹን በቦክስና በአቅራቢያው ባገኙት ነገር እየሰነዘሩ ራሳቸውን ከከፋ ጉዳት የመከላከል ተግባር ሲያከናውኑ ነበር ያለው ዘገባ በዚህ ድርጊት የተበሳጨው የቃሊቲው እስር ቤት ሃላፊ ኮሎኔል አበበ ዘሚካኤል ከእለቱ ተረኞች ውጪ የሆነ የፖሊስ ሃይል እንዲመጣለት ባዘዘው መሰረት የፖሊሱ ሃይል በእስረኞቹ ላይ የጭካኔ እርምጃ የወሰደ ከመሆኑም በላይ በዚያው ቅጽበት በአምስት አውቶብስ ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ እስረኞች ወደ ዝዋይ እንዲሄዱ መደረጋቸውን አስረድቶዋል

በእነዚሁ የወያኔ ተላላኪዎች ግፍ የተመረሩት እስረኞች ዝዋይ እስር ቤት እንደገቡ በአንድ  ቤት ውስጥ ታሽገው ያለምንም እህል ውሃ ለሃያ አራት ሰኣት እንዲቆዩ ካደረጉዋቸው በሁዋላ የቅዝቃዜው መጠን ከፍ ብሎ በረዶ በሰራ የበርሜል ውሃ ውስጥ ለሰዓታት እንዲቆሙ እና በቅዝቃዜ የደነዘዘ አካላቸውን በአጣና ጉማጅ ዱላ እየደበደቡ ለከፍተኛ ጉዳት ዳርገዋቸው ለግዜው ቁጥራቸው በውል ያልተጠቀሱ እስረኞች በዚሁ በቀዘቀዘ ውሃ እየተዘፈዘፉ መደብደብ ባስከተለባቸው ጉዳት በመኖርና ባለመኖር መሃል ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሎዋል

ይህ ዘገባ ተጠናቅሮ እስደረሰበት ዛሬ እሁድ ሰኔ 14 ቀን 2001 ዓ. ምሽት 1 ሰዓት ድረስ ቤተሰቦቻቸው ያሉበትን ቦታ አለማወቃቸውንና ሞተውም እንደሆን ሬሳ ይሰጠንና እንቅበር በማለት ጥያቄ ማቅረባቸውን ለማወቅ ተችሎዋል ።